# የሲያትል ከተማ አዲስ የስራ ሕጎች አሉት

— የሚተዳደረው በሠራተኛ መመዘኛ ጽ/ቤት ሲሆን በሲያትል ሕዝባዊ መብቶች ጽ/ቤት ውስጥ የሚገኝ ክፍል ነው —

## አነስተኛ የደሞዝ መጠን

(SMC 14.19)

— ከአፕሪል 1, 2015 ጀምሮ —

**$11.00/በሰዓት**

**ትልልቅ አሰሪ መሥሪያ ቤቶች** (501 ወይም ከዚያ በላይ ሰራተኞች)

አነስተኛ የደሞዝ መጠን፤ **$11.00**/በሰዓት

**ትንንሽ አሰሪ መሥሪያ ቤቶች** (500 ወይም ከዚያ በታች ሰራተኞች)

አነስተኛ የካሳ መጠን፥ **$11.00**/በሰዓት

**$11.00**/በሰዓት ይከፍላሉ። —ወይም—

**$10.00**/በሰዓት እንዲሁም **$1.00**/በሰዓት ከሰራተኛ ቲፖችና ወይም ብቁ ለሚሆኑ የሰራተኛ የህክምና ጥቅሞች እቅድ መክፈል።

**አነስተኛው የደሞዝ መጠን በየዓመቱ በጃንዋሪ 1 ላይ ከፍ ይላል።**

## የደሞዝ ዝርፊያ

(SMC 14.20)

**ሳይከፍሉ ሲቀሩ መከፈል ያለባቸው ደሞዞችና ቲፖች**

**የደሞዝ ዝርፊያ ሲባል፣ ሊከፈልዎ የሚገባዎን ደሞዝ ሙሉ በሙሉ አለማግኘት ነው**

- አነስተኛውን የደሞዝ ደረጃ አለመክፈል
- ለሰሩት አቨርታይም አለመክፈል።
- ከስራ ሰዓት ውጭ መስራት።
- ከነጭራሹ አለመክፈል።
- እንዲከፈልዎ ቃል የተገባልዎትን መጠን አለመክፈል።

**አሰሪ መሥሪያ ቤቶች ለሰራተኛ በጽሑፍ የተዘጋጀ መረጃ መስጠት ይኖርባቸዋል**

- ከአሰሪ ጋራ የመገናኛ መረጃ
- የክፍያ ደረጃ(ዎች)
- ጠቅላላ ደሞዝ
- ቲፕን አስመልክቶ ፖሊሲና አከፋፈል
- ተቀናሾች
- የክፍያ ቀንና የክፍያ መሰረት

እነዚህን ሕጎች የሚመለከት መረጃ በእንግሊዝኛ፣ ስፖኛ፣ እና በሌሎች በሰራተኞቹ በተደጋጋሚ በሚነገሩ ቋንቋዎች መሰጠት ይኖርበታል።

**⚠ ሰራተኞች ለሚከተሉት ምክንያቶች ለሠራተኛ መመዘኛ ጽ/ቤት ቅሬታዎቻቸውን ማሰማት ይችላሉ፤**

- አነስተኛውን የደሞዝ ደረጃ ካላገኙ።
- የደሞዞችና ቲፖች ክፍያዎችን ካላገኙ።
- ደሞዞችንና ቲፖችን አስመልክቶ በጽሑፍ የተዘጋጁ ማስታወቂያዎችን ካልተቀበሉ።
- የብቀላ እርምጃ ከደረሰባቸው።